የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

ከታህሳስ 29 - ጥር 6፤ 2017 ዓ.ም

JANUARY 7- 14, 2025 G.C


**1.የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ይፋ መደረጉ ተሰማ**

**Reporter: January 12, 2025**

ከመንግሥት የመገናኛ ብዙኃን በተጨማሪ የተወሰኑ የውጭ ሚዲያዎችና ለመንግሥት ቅርብ የሆኑ የአገር ውስጥ የግል ሚዲያዎች ብቻ እንዲዘግቡት በተደረገው፣ የኢትዮጵያን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር)ን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በተገኙበት ዓርብ ጥር 2 ቀን 2017 ዓ.ም. ይፋ ተደረገ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር) በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሠፈሩት መልዕክት፣ «ለኢኮኖሚና ለፋይናንስ ምኅዳራችን ታሪካዊ በሆነ እጥፋት፣ የኢትዮጵያን የመጀመሪያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ደወል ደውለናል። ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ባላት፣ ለብልፅግና ሰፊ ዕምቅ አቅምና ምቹ መንገድ እየተነጠፈላት ባለችው ኢትዮጵያ ሙዓለ ነዋይዎን ያፍሱ፤» በማለት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ለረዥም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓላ ገበያ ሥራ መጀመር ባብዛኛው የዘርፉ ባለሙያዎች «ታሪካዊ» በመባል የተሞካሸ ሲሆን፣ ባንኮች ሊያደርሱት አልቻሉም የተባለውን የፋይናንስ አቅርቦት ችግር በመፍታት የምጣኔ ሀብት ዕድገቱን ያፋጥናል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡

የሰነደ ሙዓለ ገበያ አክሲዮኖች፣ የዕዳ ሰነዶችና ሌላ ማንኛውም በሀብት የተደገፈ ሰነደ ሙዓለ ነዋይ ዓይነት መብት ጥቅም ወይ ሰነድ፣ በአሁናዊ ሰዓት (Real-time) እንዲሻሻ የሚያስችል፣ እስከዛሬ በኢትዮጵያ ካለው የአክሲዮኖች አሻሻጥ የተለየ በቴክኖሎጂ ብቻ የተደገፈ የገበያ ሥርዓት ነው፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/137335/

**2. የታተሙ የታክስ ደረሰኞችን ሪፖርት በማድረግ እንዲወገዱ ገቢዎች ሚኒስቴር አሳሰበ**

**Reporter: January 8, 2025**

የገቢዎች ሚኒስቴር የተሻሻለው የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም መመርያ ተፈጻሚ ከሆነበት ከኅዳር 3 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ባለው ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉና ቀደም ብሎ የታተሙ ደረሰኞች ሪፖርት ተደርገ እንዲወገዱ አሳሰበ፡፡

ሚኒስቴሩ ታክስ ከፋዮች ጥቅም ላይ ያልዋሉና ቀደም ብሎ የታተሙ ደረሰኞችን ተመዝጋቢ ለሆኑበት የታክስ ባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት በማድረግ ደረሰኞቹ እንዲወገዱ የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው፣ ታኅሳስ 26 ቀን 2017 ዓ.ም. ለግንዛቤ በሚል ባወጣው መግለጫ አስታውሷል፡፡

ኅዳር 3 ቀን 2017 ዓ.ም. የገቢዎች ሚኒስቴር በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ የግብር ከፋይ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በላከው ደብዳቤ፣ የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀምና አስተዳደር መመርያን ለማሻሻል በወጣ መመርያ ቁጥር 188/2017 መሠረት የማሻሻያ መመርያው ተፈጻሚ እንደሚሆን ማሳወቁ የሚታወስ ነው፡፡

ሚኒስቴሩ ባወደቀው መመርያ መሠረት ለእያንዳንዱ የንግድ ሥራ ዘርፍና የንግድ አድራሻ የተለያየ ደረሰኝ እንዲታተም ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን፣ በእያንዳንዱ ደረሰኝ ላይ ልዩ መለያ ኪውአር ኮድ (QR Code) ማካተት አስፈላጊ መሆኑን መደንገጉ የሚታወስ ሲሆን፣ እያንዳንዱ የደረሰኝ ቅጠል ሲታተም ልዩ መለያ ኮዱ ተካቶ ካልታተም ተቀባይነት አይኖረውም ተብሏል፡፡

ከዚህ ባሻገር ከአንድ በላይ የንግድ ሥራ ዘርፍና የንግድ አድራሻ ያለው ታክስ ከፋይ ድርጅት ከሆነ፣ የማንዋል ደረሰኝ ለማሳተም ጥያቄ ሲቀርብ ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ የሚስፈልገውን የጥራዝ መጠን መግለጽ እንዳለበት በተመሳሳይ የተደነገገ ሲሆን፣ ግለሰብ ከሆነ ደግሞ እያንዳንዱ የንግድ ሥራ ዘርፍ ለሚካሄድበት ቦታ የሚያስፈልገውን የጥራዝ ብዛት መግለጽ ይኖርበታል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/137168/

**3. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መጀመር የፋይናንስ ስርዓቱን የሚያሻሽልና አካታች ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያግዝ ነው - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)**

**ኢዜአ፡ ጥር 6/2017**

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መጀመር የፋይናንስ ስርዓቱን የሚያሻሽልና አካታች ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያግዝ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን ዛሬ በይፋ አስጀምረዋል፡፡

የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የተለያዩ የንግድ አይነቶችን ታሳቢ በማድረግ ሶስት ልዩ ልዩ የገበያ አይነቶችን የሚያቀርብ ነው፡፡

እነርሱም የአክሲዮን ገበያ፣ የዕዳ ሰነድ ገበያ እና የአማራጭ ገበያ ናቸው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በዚሁ ጊዜ እንዳሉት፤ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ስብራት ብሎም የዜጎችን ኑሮ ለማሻሻል ከተከናወኑ ስራዎች አንዱ ዲጂታላይዜሽን መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ዲጂታል ኢትዮጵያ አማካኝነትም የዲጂታል ፋይናንስ ስርዓትን ማስፋት መቻሉን ነው ያነሱት፡፡

በዲጂታል ባንኪንግ ዘርፍ የተመዘገበውን ስኬት በካፒታል ገበያ ስርዓት በመደገፍ ኢኮኖሚውን ይበልጥ ውጤታማ ማድረግ እንደሚገባም ነው ያብራሩት፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአፍሪካ ግዙፍ አየር መንገድ የሚያንቀሳቅስ፤ ግዙፍ የኃይል ግድብ እንዲሁም እንደ ኢትዮ-ቴሌኮም ያሉ ግዙፍ ኩባንያዎችን የገነባ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ይህ ግዙፍ ኢኮኖሚ ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ምቹ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያም ውጤታማ እንደሚሆን አረጋግጠዋል፡፡

በሌላ መልኩ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መጀመር ሃሳብ ኖሯቸው በገንዘብ እጥረት ምክንያት ስራ መጀመር ላልቻሉ ወጣቶችም ሃሳባቸውን አቅርበው ፋይናንስ እንዲያገኙ የሚያደርግ ስለመሆኑም አብራርተዋል፡፡

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5773565

**4. ባለፉት አምስት ወራት 617 ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቧል - የገቢዎች ሚኒስቴር**

**ኢዜአ፡ጥር 3/2017**

ባለፉት አምስት ወራት 617 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰቡን የገቢዎች ሚኒስትር ወይዘሮ አይናለም ንጉሴ ገለጹ።

በጅማ ከተማ እየተካሄደ የሚገኘው የፋይናንስ፣ የፐላንና ገቢዎች የምክክር መድረክ ዛሬ በገቢ አሰባሰብ ላይ አተኩሮ ውይይት አድርጓል።

በዚሁ ጊዜ የገቢዎች ሚኒስትሯ ወይዘሮ አይናለም ንጉሴ፤ ባለፉት አምስት ወራት ለመሰብሰብ የታቀደው 648 ቢሊዮን ብር መሆኑን ገልጸው 617 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰብ መቻሉን ተናግረዋል።

ይህም ለመሰብሰብ ከታቀደው 95 በመቶ መሆኑን ገልጸዋል።

የበጀት ዓመቱን እቅድ ለማሳካትም የገቢ ሰብሳቢ ተቋማት የደረሰኝ ማጭበርበርንና የታክስ ስወራን መከላከል ላይ በትኩረት እንዲሰሩም አሳስበዋል።

በተጨማሪም የግብር ከፋዩን ግንዛቤ ማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎችን ማጠናከር፣ የገቢ አሰባሰብ ሂደቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማገዝም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ነው ያሉት።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5777229

**5. AU Adopts Agricultural Development Strategy for Next Decade**

**ENA: January 12, 2025**

African nations on Saturday adopted a new strategy to advance agricultural development and food systems, a The 10-year strategy and action plan to implement the Comprehensive Africa Agriculture Development Program (CAADP), along with a consensus document titled the Kampala Declaration, were announced on Saturday at the conclusion of the African Union Extraordinary Summit on CAADP in Kampala, the capital of Uganda.

Under the new framework, African countries committed to intensify sustainable food production by increasing agri-food output by 45 percent by 2035 and reducing post-harvest losses by 50 percent.

They also agreed to boost investment and financing in the agricultural sector, aiming to raise 100 billion U.S. dollars in public and private investments by 2035.

To achieve these goals, African countries urge collective commitment from governments, parliaments, food producers, the private sector and civil society to translate decisions into tangible results.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5779942

**6. New coffee strategy aims to position country as second-largest global coffee exporter by 2033**

**Capital: January 13, 2025**

The new coffee strategy and roadmap aim to position Ethiopia as the world's second-largest coffee bean exporter within eight years, while also increasing the country's hard currency revenues by more than six times. Ethiopia, known as the birthplace of coffee and home to over 10,000 distinct varieties, currently earns relatively little from this vital industry, despite coffee being one of the most traded commodities globally. Since coffee was first discovered in the ninth century in Keffa, located in western Ethiopia, it has been marketed internationally and is commonly regarded as the second most traded commodity by volume, following crude oil. The Ethiopian Coffee and Tea Authority (ECTA), established in 2016, has initiated several projects to promote the marketing and development of the coffee industry. Prime Minister Abiy Ahmed has projected that Ethiopia will rank among the top coffee exporters in the coming years.

https://capitalethiopia.com/2025/01/13/

**7. Fuel subsidies drive price stabilization fund debt to 133 billion birr**

**Capita : January 13, 2025**

The Ethiopian government's fuel subsidies have significantly increased the debt of the Price Stabilization Fund, now totaling 133 billion birr over the past five months, according to the Petroleum and Energy Authority. Of this amount, 30 billion birr is attributed to subsidized payments, highlighting the growing financial strain on the government.

Sahrela Abdullahi, Director General of the Petroleum and Energy Authority, presented these figures during a session of the House of People's Representatives. He noted that the failure to adjust oil prices in recent years has severely depleted the funds originally allocated for price stabilization. The fund's reserves have dwindled from 58 billion birr to 133 billion birr in just five months of the current fiscal year.

Sahrela explained that despite stable global oil prices, the government's losses have escalated. He stated, "The loss of 58 billion birr in July 2016 has now risen to 133 billion birr due to increasing debt from fuel subsidies." This alarming trend was discussed during a session where lawmakers adopted a new bill aimed at regulating the trading system for petroleum products.

https://capitalethiopia.com/2025/01/13/

**8. Court orders injunction on Addis Chamber's controversial election plans**

**Reporter: January 11, 2025**

A judge at the Federal First Instance Court has placed an injunction order on the Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Associations (AACCSA), freezing plans by President Mesenbet Shenkute and other members of senior management to hold elections during an upcoming general assembly.

Judge Gerawerk Yitbarek of the Court's Trade and Investment Bench signed the order, which will remain in place until the Chamber's members and management can come to an amicable solution to a dispute involving sudden changes to the organization's election bylaws.

Chamber management, led by Mesenbet, recently called a general assembly in order to hold elections without the involvement of the Chamber's candidate screening committee, which is a breach of the organization's rules, according to the plaintiff.

The Chamber's regulations state an election can only move ahead after candidates have been approved by the election credential committee. However, Mesenbet and other senior leaders recently scrapped the committee. The development came as the Chamber prepared to organize its critical but much-delayed general assembly and election.

The vote would mark the end of Mesenbet's term at the head of the organization.

https://www.thereporterethiopia.com/43316/